# በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት

# የወላይታ ዞን አቅም ግንባታ

# መምሪያ የ2001 ዓ.ም

# <u>ክንውን ሪፖርት</u>

ሰኔ 2001

<u>ሶዶ</u>

## መግቢያ፡-

በዞኑ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና የማስፈፀም አ/ግንባታ ኘሮግራሞችን በተቀናጀ ሁኔታ ለማከናወን በሴክተሩ መሠራት የሚገባቸውን ቁልፍ የትኩረት መስኮችን በመለየት ግቦችን በማስቀመጥና ለግቦቹ ውጤቶችንና ስኬት አመለካችን በማካተት የዘመኑን የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ወደሥራ መግባቱ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም በሥራ ዘመኑ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ/BPR/ ቋሚ ትግበራ ውስጥ ከገቡት 7 ሴክተሮች መምሪያ አንዱ ስለሆነ ሥራዎችን በ4 ዋና እና በ2 ደጋፊ የሥራ ሂደቶች በለውጡ አሠራር በመቃኘትና ዕቅዱን በመከለስ ወደ ትግበር በመግባቱ ካለፉት ዓመታት አፈጻጸም የሴክተሩ የሥራ ዕቅድ አፈጻጸም የተሻለ ውጤት ያስመዘገበ ሲሆን ዝርዝር አፈጻጸሙ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## I) በለውጥ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶች አንጻር

### 1. ከሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም አንጻር

11. በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ

- የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት አጠናቀው ወደ ሙሉ ትግበራ ለገቡ ለ7 ሴክተሮች እስከ ወረዳ/ከተማ/ ሴክቴሮች ድረስ የቴክኒክና የምክር ድጋፍ ለመስጠት በታቀደው መሠረት አስፈላጊው ድጋፍ ተሰቷል፡፡
- በ BPR አተገባበር ላይ ለ7 ሴክተር መ/ቤቶች ሠራተኞችና ኃላፊዎች ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ የ6ቀናት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና በክልሉ በኩል ተሰቷል፡፡
- BPR ተግባራዊ ባደረጉ በሰባቱ ሰክተር መ/ቤቶች ስለውጤት ተኰር ዕቅድ አተገባበር ድጋፋዊ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ እስከ ወረዳና የከተማ ሴክተሮች ድረስ አስፈላጊው ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡
- የ BPR ሙሉ ትግበራ ውስጥ ያልገቡ በጥናቱ ላይ ለነበሩ ለ8 ሰክተሮች የውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓት ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

1.2 በአገልግሎት አሰጣጥ አንጻር

- የአገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲን በተጠናከረ መልኩ በሁሉም የመንግሥት ተቋማት ለመተግበር

  - ከዞን እስከ ወረዳ ባሉት የመንግሥት መ/ቤቶች የአገ/አሰጣጡ እንድለወጥ የ Quick wins ሥራዎች ተጠናክረው እንድሠሩ 90% ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ 95% ድጋፍ ተሰጥቷል።

  - ለሲቪል ሰርቫንቱም የሕዝብ አገልጋይነት ስሜት እንዲፈጠር ለሁሉም መንግሥት ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

- የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ ውጤታማ ለማድረግ 7ቱም ሰክተሮች የተገልጋይ አስተያየት መቀበያ መድረክ በመፍጠር እንድተገብሩ 100% ድጋፍ ተሰጥቷል።

1.3. ከበላይ አመራር ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም አንጻር

- በስትራቴጂክ ዕቅድ አመራር በዓመታዊ ዕቅድና በውጤት ተኮር ዕቅድ አሠራር ሥርዓት ከዞን እስከ ወረዳ /ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ በየሴክተሮች ሥርዓቱን በመከተል ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ ተሰጥቷል።

## 2. ከፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ አንጻር

2.1. የከፍተኛ ፍ/ቤቶች ማሻሻያ ኘሮግራም በተመለከተ

- ለሕብረተሰቡ ፋጣንና ቀልጣፋ ለመስጠት ከፍትሕ አካላት ጋር በመቀናጀት ለመሥራት ከተዘረጋው ሥርዓት አንጻር የፍርድ ቤቶችን ተደራሽነት ቀጣይነት ባለው መልኩ እንድሠራና እጅ ከፍንጅ ለተያዙ ወንጀለኞች የዕለት ፍርድ ውሣኔ አሰጣጥ ሥርዓት እንድኖር ድጋፍ ለሁሉም ወረዳዎችና ከተሞች እንዲሁም ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ተደርጓል።

- መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ቋሚ ትግበራን በከፍተኛ ፍርድ ቤት ፣ በወረዳ ፍርድ ቤቶችና በከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ከሐምሌ 1 2001 ዓ.ም ለመጀመር የቅድመ ዝግጅት ሥራ ተጠናቋል።

ይኸውም ቢሮች ለሥራ ሂደት በሚመች መልኩ ተዘጋጅተዋል፤ ቁሳቁሶች ተደራጅተዋል፤ የሰው ኃይል ዝግጅት ተጠናቋል።

- በዞኑ በሁሉም ወረዳዎች ተዘዋዋሪ ችሎት ማስቻያ ቦታዎች ተዘጋጅተዋል። ለሕብረተሰቡ ቅርብ በሆነ አከባቢ የዳኝነት ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።
- በዞኑ በሁሉም 288 ቀበሌያት የማኀበራዊ ፍርድ ቤቶች በተሰጣቸው ሥልጣን ለሕብረተሰቡ ፍትሕ እየሰጡ ይገኛሉ።

2.2. ፖሊስ ማሻሻያ ኘሮግራም በተመለከተ

- የኀብረተሰቡን ሰላምና ጸጥታ ለመጠበቅግ ፈጣንና ፍትሐዊ አገልግሎት ለመስጠት በሁሉም ከተማና ገጠር ቀበሌያት የኮሚኒቲ ፖሊስንግ እንዲጠናከር በታቀደው መሠረት በ288 ቀበሌያት የኮሚኒትንግ ፖሊሲ ምክር ቤት ተቋቁሟል።
- በዚሁ መሠረት ለ800,000 የኀ/ሰቡ ክፍሎች በተለያዩ ርዕሶች የኮሚኒቲ ፖሊስንግ ሥልጠና በሴክተሩ በኩል ተሰጥቷል።
- ከሳንተሪያ ጥበቃ ረገድ በዞኑ 1060 ሳንተሪያዎች እንድቋቋሙ ተደርጓል። ከእነዚህ 900 አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ሌሎቹ እድሣት የሚያስፈልጋቸው ናቸው። በዚህ የኀብረተሰቡ ደኀንነት ከመጠበቅ አንጻር ዞኑ የክልሉ ቢሎም የሀገር ተምሣሌት ሆኗል።
- ከኮሚኒቲ ፖሊስንግ አፈጻጸም አንጻር ለምሣሌ በዳሞት ወይዴ ወረዳ በኪንዶ ኮዮ ቀበሌ እና በኪንዶ ኮይሻ ወረዳ በሶርቶ ቀበሌ ለምርጥ ተሞክሮ የሚሆኑ ተግባራት እየተፈጸሙ ይገኛል።

2.3. የዐቃቤ ሕግ ማሻሻያ ኘሮግራም በተመለከተ

- የከሳሽ መርማሪ ሥራ ሂደት ከሐምሌ 1/ 2001 ዓ.ም ጀምሮ ቋሚ ትግበራ ለማከናወን በክልል የተሰጠው የአሰልጣኞች ሥልጠና በመሰልጠን በዞን ደረጃ በሥራ ሂደቱ ለተመደቡ ባለሙያዎች ሥልጠና ለመስጠት ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል።
- በዞኑ ውስጥ ለወንጀል ጠቋሚዎች የሕግ ጥበቃና ከለላ ከማድረግ አንጻር ለምስክሮች ተገቢው የሕግ ከላለ እየተደረገላቸው ይገኛል።
- የንጹሐንን መብት የሚያስገፍፍ በሐሰት መስካሪ ግለሰቦች በሕግ ተጠያቂ የሚያደርግ አሠራር ሥርዓትን ተግባራዊ ከማድረግ በኩል በዞኑ በሁሉም ወረዳና ከተማ የውሸት መስካሪዎች በሕግ በማቅረብ ተገቢ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል።
- በሥራ ዘመኑ በሴክትሩ ተጣርቶ ውሣኔ ያገኘ መዝግብ ብዛት 8371 ሲሆን ዉሳኔ ያላገኘ መዝገብ ብዛት 2016 ነው።

- ውልና ማስረጃ ከዚህ በፊት በየወረዳና ከተማ የሚሰጠው በአሁን ወቅት በBPR ጥናትና ትግበራ መሠረት በዞን ማዕከል በመስተናገዱ ከዚህ ሥራ ሂደት ከሚገኝ ገቢ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፡፡
- በወንጀል ክስ ማስረጃ አቅራቢዎች ወይም ምስክሮች በራስ ወጪ መጓጓዝን በመንግሥት ለመሸፈን በታቀደው መሠረት ዞኑ ብር 60,000 መድቦ ከመንግሥት ወጪው እንድሸፈን ተደርጓል፡፡

2.4. ከማረሚያ ቤቶች ማሻሻያ አንጻር

- በማረሚያ ቤት የተለያዩ ማሻሻያ ሥልጠናዎች ተሰጥቶ የሕግ ታራሚዎች የሙያ ሥራዎች ተጠቃሚዎች ከመሆናቸው በተጨማሪ መደበኛ ትምህርት ለሌላቸው 1ኛ-4ኛ ክፍል መደበኛ ትምህርት በማረሚያ ተቋም ግቢ ተከፍቶ እየተማሩ ይገኛሉ፡፡
- የታራሚዎች የሕክምና አሰጣጥ የሕክምና ባለሙያዎች ተቀጥሮ የሕክምና አገልግሎት በመስጠትና የመድኃኒት አቅርቦትም በተሻለ ሁኔታ ይገኛል፡፡

## 3. የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር

. ከዞን እስከ ቀበሌ ድረስ የዕቅድ የኢንስፔክሽንና የሱፔርብዥን ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

. ለዚሁ ሥራ የሚያገለግል የዕቅድ የኢንስፔክሽንና የሲፐርቪዥን ማስፈጸሚያ ማኑዋል ተሰራጭቷል፡፡

. በሁሉም የወረዳ ቀበሌያት ለተቀጠሩ ለ288 የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለሁሉም ሥራ አስኪያጆች የተሃድሶ ሥልጠና ተሰጥቶ ወደተሟላ የሥራ እንቅስቃሴ እንድገቡ ተደርጓል፡፡

. እንዲሁም ወደ ገጠር ቀበሌ የሚወርዱ የገጠር ልማት ተግባሮች በቀበሌ ደረጃ ተጣምረውና ተቀናጅተው ወደ መሬት እንዲወርዱ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

- ሕብረተሰቡን በግልና በጋራ ሥራ የማሳተፍና አሣምኖ የማሠራት ሥርዓት ለመዘርጋት በታቀደው መሠረት በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የሞዴል አርሶ አደሮች ምርጫ እንድከናወንና የተመረጡትም የመሪነት ሚና እንዲጫወቱ የሚያስችል የምክርና የቴክኒክ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

- በሁሉም የዞኑ ወረዳዎች በሕብረተሰቡ ውስጥ በግልና በጋራ ሥራ ሞዴል የሆኑ ተግባራትን ያከናወኑ ሞዴል መንደሮችና ቀበሌዎች ምርጫ እንዲካሄድ ተደርጓል።

## II) በኢኮቴ መሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት የሥራ ሂደት የተከናወኑ

- የአሠራር ሥርዓት ጥናት /BPR/ ለተገበሩ የሥራ ሂደቶች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ከመደገፍ አንፃር በሁሉም ወረዳዎችና ከተሞች ባሉ በሰባቱም ሴክተር መ/ቤቶች በዘመናዊ የኢንፎርመሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ ድጋፍ ተሰጥቷል።
- በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት በማስፋፋት በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማፍራት አንፃር በመሠረታዊ የኮምፒዩተርእና የኢንቴርነት አጠቃቀም ለ200 ሠራተኞች ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ 231 ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።
- በ7ቱ ነባር ወረዳዎች የተቋቋሙትን የቪዲዮ ኮንፍራንስንግና የመረጃና የመገናኛ ማዕከላት ሥራ ለማጠናከር ድጋፍ ለመስጠት በታቀደው መሠረት የተሟላ የድጋፍ ሥራ ተሰርቷል።
- ለ12 ወረዳዎችና 3 የሪፎርም ከተሞች እንዲሁም ለዞን መምሪያዎች የኢኮቴ የቴክኒክ ድጋፍና የጥገና አገልግሎት ተሰጥቷል።

## III) በሰው ሀብት ልማት የተከናወኑ

- በዞን በወረዳና በከተማ ደረጃ ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም ለመገንባት ከክልሉ በተሰጠን ኮታ መሠረት በ2ኛ ዲግሪ 8 በመጀመሪያ ዲግሪ 28 ሠራተኞችንና አመራሮችን በመመልመል ለመግቢያ ፈተና እንዲቀርቡ ተደርጓል።
- የወረዳ አቅም ግንባታ ኘሮግራሞች ዙሪያ ከወረዳ ከከተማና ከዞን መምሪያ ለ47 ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ለ3 ተከታታይ ሳምንታት የአሠልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።
- በ12 ገጠር ወረዳዎች ለቀበሌ ሥራ አስኪያጆችና አመራር አካላት ፡- በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ መርሆችና አተገባበር
- በኘሮጀክት ጥናት እቅድ ዝግጅት ትግበራ ክትትልና ግምገማ ሥልጠና በመረጃ አያያዝ ላይ ሥልጠና ተሰጥቷል።

## IV) በሰው ሀብት ሥራ አመራር የተከናወኑ

- በአዲሱ የሥራ ሂደት ለውጥ የሰው ሀብት ሥራ አመራር በመምሪያችን ዋና የሥራ ሂደት ሆኖ ስለተጠና በሌሎቹ ሰክተሮች ድጋፍ የሥራ ሂደቱ በመሆኑ በሥራ ሂደቶቹ ለተመደቡ ከዞን እስከ ወረዳ/ከተማ ስክቴሮች ለተመደቡ 270 ሠራተኞች ለማሰልጠን ታቅዶ ለ120 ሠራተኞች የ6 ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ክንውኑ ሊያንስ የቻለው በአብዛኛው ሰክተሮች ላይ በሥራ ሂደቱ የሠራተኛ ምደባ ባለመሰጠቱ ምክንያት ነው፡፡
- በሰክተሩ ክፍት በሆኑ መደቦች ላይ በቅጥር ለማሟላት በታቀደው መሠረት 3 ሠራተኞችን በቅጥር 1 ሠራተኛ በምደባ በድምሩ 4 ሠራተኞችን የማሟላት ሥራ ተሰርቷል፡፡
- የደጋፊ የሥራ ሂደት ከሰክተሩ የሥራ ባህሪይ ጋር በማጣጣም የሥራ ሂደቱን ሥራ በጥናቱ ሰነድ መሠረት ማከናወነ እንዲችሉ ከዞን መምሪያዎች እስክ ከተማ/ወረዳ ሰክተሮች ድረስ የድጋፍና ክትትል ሥራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም የሰው ሀብት የማሟላት መመሪያና ሌሎች ደንቦችን ለማሠራጨት ተችሏል፡፡

## V) በመረጃ መሰብሰብና ማሠራጨት አንጻር

- ከዞን ፋ/ኢ/ልማት መምሪያ በተላከው የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ መሠረት ለ17 ሴክተሮች መ/ቤቶች፣ ለ2ቱ የቴክኒክና ሙያ ፣ ለሶዶ የአፈር ምርምር ተቋም፣ ለሶዶ ግብርና ኮሌጅ፣ ለሶዶ ሆስፒታል እና ለ12 ወረዳዎችና ለ3 የሪፎር ከተሞች ቅጽ እንዲደርስ ከተደረገ በኋላ አስፈላጊው መረጃ እንደገና በመሰብሰብ የማጠናቀር ሥራ ተሰርቷል፡፡

## VI በHIV/ADS እና ሥርዓተ ጾታ ሚንስትሪሚንግ ሥርዓት በተመለከተ

- ከዞን እስከ ወረዳ ለ60 ባለሙያዎች በHIV/ADS እና ሥርዓተ ጾታ ሚንስትሪሚንግ ዙሪያ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ30 ባለሙያዋች በሴቶች ልማትና የለውጥ ፓኬጅ ላይ የማስተዳደር አቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

- በHIV/ADS እና ሥርዓትተ ጾታ ሚንስትሪሚንግ ዕቅድ በተቋሙ ሥራ ዕቅድ እንድካተት ተደርጓል፡፡
- በዞኑ ከHIV/ADS እና ሥርዓተ ጾታ ሚንስትሪሚንግ ኮሚቴ ጋር ተቋሙን በመወከል የድጋፍና ክትትል ሥራዎች ዙሪያ እገዛ ተደርጓል፡፡
- ከመ/ቤታችን ሠራተኞች ከHIV/ADS ጋር ላሉ ወገኖች ድጋፍ የሚሰበሰብ 0.5% ገንዘብ መዋጮ ሳይቋረጥ ገቢ እንዲደረግ ተገቢ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

## ያጋጠሙ ችግሮች

ሴክተሩ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የተለያዩ ችግሮች ያጋጠሙን ሲሆን ከእነዚህ ዋና ዋናዎቹ፡

1. የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ ውጤታማ ለማድረግ በየደረጃው የሚገኘው አመራር የBPR ሥልጠና ባለመወሰዱ ለውጡን በባለቤትነት ስሜት አለመምራት ጉድለት ጉልቶ መታየት፣
2. የሠራተኞች ድልድል በደንብ ቁጥር 72/2001 መሠረት በየአካባቢው ባለመፈጸሙ የአቤቱታዎች የቅሬታዎች ቁጥር መበራከት፡፡
3. የአ/ግንባታ ሥራ መንግሥታዊ ተቋማትን ከዞን መምሪያዎች እስከ ቀበሌ ድረስ ወርዶ በመደገፍ የማብቃት ሥራ ሲሆን ለዚህ ሥራ እንቅስቃሴ ከፍተኛ የበጀት እጥረት ማጋጠሙ፣
4. BPRን ተግባራዊ ለማድረግ አጋi የሆነውን የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኒዮሎጂ አገልግሎት በየተቋማት ለመስጠት የኮሚፒዩተሮችና የተለያዩ የICT ማቴሪያሎች እጥረት መኖር
5. የሴክተሩን ሥራ በበቂ ሁኔታ ለማከናወን የቢሮ ቁሳቁስና የቢሮ እጥረት መኖሩ
6. በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በምደባ ላልተካተቱ ሠራተኞች አማራጮችን ተግባራዊ ለማድረግ የአፈጻጸም መመሪያዎች መዘገየት፣

## የተወሰዱ መፍትሄዎች

- አመራሩ በBPR ግንዛቤ እንዲያገኝ በክትትልና ድጋፍ ወቅት በመከታተያ ቼክ ሊስት ላይ ግንዛቤ ማስጨበጡ
- ምደባ ያላገኙ ሠራተኞችን መምሪያዎች፣ወረዳዎችና ከተሞች በደንብ ቁጥር 72/2001 መሠረት እንዲመደቡ በየጊዜው ድጋፍ መደረጉ
- ለክትትል እና ድጋፍ ሥራ የበጀት እጥረት ቢኖርም በመቀናጀት በተመደበው በጀት ከሞላ ጎደል ለመሥራት መቻሉ፤
- የICT ማቴሪያሎች እጥረት አሁንም መፍትሄ አላገኘም፡፡
- የቢሮ እጥረትን በተመለከተ ባሉት ክፍሎች በመጣበብም ተጠቅመን ስንሠራ መቆየት፡፡
- ምደባ ያላገኙ ሠራተኞችን በተቀመጡት አማራጮች ለማስተናገድ ዝርዝራቸውን ከየወረዳ ከተማና ሥራ መምሪያዎች ተሰብስበው ተጣርተው እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡